# የሕዳሴው ጉዞና ያስከተለው መነቃቃት

ሃይለ ከበደ 8/10/12

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ምንጭ ፣የጥንታዊ ስልጣኔ ና የተለያዩ አየር ንብረት ክልሎች ባለቤት ናት፡፡ከዚህም ጋር ተያይዞ ከብዙ ዘመን በላይ ነጻነትዋን ጠብቃ የኖረች፣ በጀግኖች ልጆችዋ ክንድ ወራሪዎችን እያሳፈረች የመለሰች፣ ካልነኩአቸው ማንም ላይ የማይደርሱ ህዝቦች ሀገር ናት፡፡ ከዳማት ስርወ መንግስት በሁዋላ የአክሱም ስርወ መንግስት ተመስርቶ በኢኮኖሚና ወታደራዊ አቅሙ እጅግ የጎለበተ በወቅቱ ኃያላን ከነበሩ ከሮማውያንና ፋርስ ነገስታት ጋር ተፎካካሪ መንግስት እንደነበር ፣ታሪክ ያስረዳናል፡፡ነገር ግን ከአክሱም ውድቀት በኋላ በሀገሪቱ የነበሩት ነገስታትና መኳንንት የስልጣን ሽኩቻዎች በተደጋጋሚ በተቀሰቀሱ የእርስ በእርስ ውጊያዎች የጦር አውድማ በመሆኗ ህዝቡ ሰላምና ደህንነት ከማጣቱም በላይ የርሀብ ድንቁርናና ኋላቀርነት ተምሳሌት ሊሆን ችሏል፡፡ የንጉሳዊ ስርወ መንግስታቱ ለዙፋናቸው መደላደል እንጂ ለህዝቡ የፈየዱት ነገር ባለመኖሩ በ 1966ዓ/ም በሀገሪቱ በተቀሰቀሰው ህዝባዊ አመጽ የንጉሳዊ ስርወ መንግስት አገዛዝ ስርአተ ቀብር ለመጨረሻ ጊዜ ቢፈጸምም ስልጣኑን ደርግ ተቆጣጥሮ አምባገነናዊ ስርአት በማስፈኑ ዳግም ሀገሪቱ ለማያባራ ጦርነት ተዳርጋ ቆይታለች፡፡

በአንድ በኩል "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!" በሌላ በኩል "አብዮታዊት እናት ሀገር ወይም ሞት! አንድ ሰው አንድ ጥይት እስኪቀር እንዋጋለን!" ሲል የነበረው ደርግ በግንቦት ወር 1983 ዋከባ በዝቶበት ነበር፡፡ በሄደበት አውድ ሁሉ ሽንፈት እየገጠመው ከመቸገሩም በላይ የመላው የሰሜን አርሶ አደር እሱ "ወንበዴ" የሚላቸውን ኃይሎች መንገድ እየመራ ማስገባቱ ተስፋውን አስቆርጦታል፡፡ ግንቦት 13 ቀን ሀገር ጥሎ በኬንያ ሲሸሽ ሰራዊቱም መሳሪያውንና ልብሱን በሲቪል ጨርቅ እየለወጠ መኮብለል ጀመረ፡ ፡ ሰራዊቱ ሲሸሽ እግር እግሩን ተከትለው ግንቦት 20/ 1983 አዲስ አበባ የገቡት ታጋዮች ያጎፈሩ፣ቁምጣ ያጠለቁ፣ ሲያዩአቸው የሚያሳዝኑ የአርሶ አደሩ ልጆች ሲሆኑ እውን እነዚህ ተዋግተው አሸነፉ ለማለት አያስደፍሩም ነበር፡፡ሲቀርቧቸው ግን ትጥቃቸውም ንግግራቸውም አንድ አይነት ማንንም የማይነኩ፣ የሰው ሀቅ የማይፈልጉ፣ ሰውን ሁሉ አክባሪነታቸው ሲታይ ለዚህ ያበቃቸው ታላቅ ጽናትና አላማ እንዳነገቡ ያስታውቃሉ፡፡ ያነገቡት መርህ ቃል ግን እዚህ ላለነው ለማናችንም ቢሆን አስደንጋጭ ነበር "የብሄር ብሄረሰቦች መብት እስከ መገንጠል፣በህዝቦችዋ መፈቃቀድ አዲስትዋን ኢትዮጵያ እንገነባለን!" የሚል ነበር፡፡ማንም ደግሞ በብሄር ብሄረሰቦች መፈቃቀድ አዲሲትዋን ኢትዮጵያን እንገነባለን ሚለውን ዐረፍተ ነገር ከግምት ሳያስገባ የብሄር ብሄረሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚለውን ብቻ ይዞ ሀገሪትዋ ተገነጣጠለች ብሎ ፈርቶ ነበር ፡፡በተለይ በየበረሀው ያለ ተቃዋሚ ድርጅት አነግም ጭምር በሰላም ተገኝቶ የጋራ ስምምነት ውል ቻርተሩ ሲፈረም ይህ መሪ ቃል መቀመጡ ብዙዎችን ምሁራኖቻችንን ግራ አጋብቶ ነበር፡፡

ኢህአዴግ "ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ" በሚል አጀንዳ ሀገሪቱን በማረጋጋትና የራስ አስተዳደርን በማስፈን ክልሎች በራሳቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲጠቀሙ በማድረግና የመድበለ ፓርቲ ምርጫ ስርአት በመዘርጋት የተሻለ መልካም አስተዳደርን የማስፈን ስራዎችን ሰራ፡፡ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት፣ አለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች፣ የሴቶችና ህጻናትን መብቶች የሚያስከብር ህገ መንግስት በማውጣትም የሁሉንም መብት በእኩልነት እንዲታይ ከማድረጉም በላይ የፌዴራል መንግስቱንና የክልሎችን ስልጣን ለይቶ ገደብ በማበጀቱ፣ አንዱ ያንዱን መብት እንዳይነካ በማድረጉ፣ ክልሎች የራሳቸውን አካባቢ እንዲያለሙ በማስቻሉና ፌደራል መንግስቱ ደግሞ ከክልሎች አቅም በላይ ያለውን ማልማት በመቻሉ በመላው ሀገሪቱ ባጭር ጊዜ ሰፊ የመሰረተ ልማት ግንባታ ማዳረስ ተችሏል፡፡

መንግስት ግልጽ የትምህርት፣የጤና፣የግብርናና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎችን በመንደፍ በሀገር ውሥጥ የትምህርትን ስርጭት በማስፋፋትና በመከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ስትራቴጂ በመከተል እንዲሁም በግብርና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ በመጠቀም ውጤታማ አፈጻጸም በማምጣት፤ሰላማዊና ፍትሀዊ የጋራ ተጠቃሚነት ላይ ያጠነጠነ አለም አቀፍ ግንኙነት በመፍጠር ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ መድረክ ያላትን ሚና ማጎልበት ችሏል፡፡ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት በሰላም አብሮ በመኖር መርህ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ

ግጭቶች እንኳን ቢከሰቱ በጠረጴዛ ዙሪያ በመፍታት ስለሚያምንና ለዚህም ጠንክሮ ስለሚሰራ የጎላ የድንበር ችግር አልታየም፡፡ካለ አንድ የእብሪት ወረራ በቀር፡፡

በኢትዮጵያ ትከሻ ታዝሎ መኖር የሚፈልገው ጦረኛው የኤርትራው የሻእቢያ መንግስት ሀገሪቱ እያሳየች ያለው እመርታዊ ለውጥ ስላስጨነቀው ምክንያት አልባ የእብደት ወረራ ቢፈጽምብንም ለሰላም ካለን ጉጉት አንጻር ድንበራችንን ይዞ እያለ ለሁለት አመት ወደ ሰላሙ ከመጣ በሚል  በትግስት ሲጠበቅ ነበር፡፡ነገር ግን ጉዳዩ የጸረ-ልማት አስተሳሰብ የወለደው፣ ምቀኝነት ያነሳሳው የእብደት ወረራ በመሆኑ ይኸውም "በትግራይ የሚሰሩ ልማቶች በኤርትራ የተቀበሩ ቦምቦች ናቸው" በማለት ጠቅላላ የኢትዮጵያን ዕድገት ለማኮላሸት ታስቦ የተወሰደ በመሆኑ ምንም አይነት የዲፕሎማሲ ቋንቋ ስለማይገባው በመረጠው የጦርነት ቋንቋ በማነጋገር ባጭር ጊዜ ውስጥ ወሳኝ ድል ቢገኝም ለብዙ ዜጎች መስዋእትነትና ለልማቱ መጓተት ምክንያት ሆኖ አልፏል፡፡

መንግስት ወዲያውኑ ፊቱን ወደ ልማት በማዞር በጦርነት የወደሙትን ቦታዎች በመጠገንና ተጀምረው የነበሩ የልማት ስራዎችን ሙሉ ለሙሉ በማስቀጠል ህዝቡን ለልማት በማነሳሳት በገጠርም ሆነ በከተሞች ለውጥ ማምጣት ተችሎአል፡፡በተለይ ባለፉት ስምንት አመታት ተከታታይ ፈጣን እድገት በማምጣት ሀገራችን 11 በመቶ  አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ችላለች፡፡ከዚህም ጎን ለጎን ጤና ጣቢያዎች፣ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች፣ የግብርና ና ምርት ማሻሻያ ተቋማት፣ ወዘተ…በየትኛውም የሀገሪቱ ክልሎች የተቋቋሙ ሲሆን ፍትሀዊ የሀብት አጠቃቀምና ፍትሀዊ የልማት ተጠቃሚነት በመረጋገጡ በሁሉም ክልሎች ልማቱ ሊስፋፋ ችሏል፡፡ይህ ሁለንተናዊ ዕድገት በተከታታይ በመቀጠሉ በራሳችን አቅም የማደግ ተስፋችንን በማለምለሙ ሀገራችን ለብዙ ዘመናት ከተኛችበት በመንቃት በመታደስ ላይ በመሆንዋ ዘመኑ የኢትዮጵያ ህዳሴ ዘመን በማለት ተዋጅቷል፡፡

ዘመነ ህዳሴ ተመጣጣኝ ቃሉ የላቲን ሬኔሳንስ የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም እንደገና መወለድ ማለት ነው፡፡በአውሮፓ  ለሺ አመት ተቀብሮ የነበረው ግሪኮ ሮማን ስልጣኔ እንደገና በ13ኛውክፍለ ዘመን  ያውም እጅግ ተሻሽሎ በመወለዱ ነው እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ሬኔሳንስ ተብሎ ሲጠራ የነበረው፡፡በዚህ ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ስነ ጥበብ ከፍተኛ የእድገት ዘመን ላይ የደረሰበት፣የህክምና ሳይንስ ያደገበት፣የተፈጥሮና ማህበራዊ ሳይንስ የመጠቀበት ዘመን ሲሆን ከ3ኛው እስከ 13ኛው ክ/ዘመን/ ጭለማው ዘመን/ሊወገድ ችሏል፡፡በዚህም የተነሳ ይህን ዘመን የሰብአዊነት፣ የብርሀን፣…ወዘተ ዘመን በማለት ይጠሩታል፡፡በዚህ ዘመን የተሰሩ ጥበብ የተሞላባቸው ቤተ መንግስቶችና ቤተ መቅደሶች እንዲሁም ቀለም ቅብ ስራዎች እስከ ዛሬም ድረስ ተወዳዳሪ የሌላቸው እጅግ ረቂቅ ሲሆኑ እነ ሚካኤል አንጀሎ፣ሊዮናርዶ ዳቪንቺ፣ጋሊሊዮ ጋሊሊ፣ኮፐርኒከስ፣ዳንቴ፣ጉተንበርግና …ወዘተ ታላላቅ ሊቃውንት፣ የስነጽሁፍና የፈጠራ ሰዎች የተገኙበት ዘመን ነው፡፡

ኢትዮጵያም ከ2000 ሚሊኒየም በአልዋ መከበር በኋላ በሀገሪቱ የታየውን ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገትና በሀገር አቀፍ ደረጃ የታየውን የዲሞክራሲና የማህበራዊ እድገት በመገምገም በታሪካችን ያልደረስንበት ደረጃ ላይ እንደምንገኝና ይህ የተፈጠረው ሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ በሀገሪቱን የህዳሴ /ሬኔሳንስ/ ጅማሬ መሆኑን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አበሰሩን፡፡ታዲያ በዚህ የህዳሴያችን ዘመን ሀገራችን በስነጥበብ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣በፈጣን ኢኮኖሚ እያስመዘገበችው ያለው ለውጥ በህዘብ የነቃ ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ሁሉም ለህዳሴው እንዲተጋ ለማድረግ መንግስት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመንደፍ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ በዚህ እቅድ የተቀመጡት የልማት ስራዎች በጣም ግዙፍና ሰፋፊ ሲሆኑ በኢትዮጵያ አቅም ሊሰሩ የማይችሉ ናቸው በማለት አንዳንድ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች የተቹት ቢሆንም መንግስት በህዝባዊ ተሳትፎ የማይቻል ነገር የለም በሚል ጽኑ ህዝባዊ እምነት ጉዞውን ቀጥላል፡፡ከነዚህ ታላላቅ ግንባታዎች አንዱ በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ግድብ ሲሆን ከግድቡ ትልቅነትና አስፈላጊነት እንዲሁም ታሪካዊነት አንጻር የታላቁ ህዳሴ ግድብ /Great Renaissance Dam/ የሚል ስያሜ በመስጠት መጋቢት 24 2003 ዓ/ም ግንባታው መጀመሩ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተበሰረ፡፡ዜናውን የሰማ ኢትዮጵያዊ ሁላ በደስታ ድጋፉን ሲሰጥ ምንነካቸው የማይችሉትን ነገር ይዘባርቃሉ ያሉም አልጠፉም፡፡ በህልውናችን መጡ ብለው ቅር ያላቸውም ሀገሮች ነበሩ፡፡ነገር ግን

ሁሉም የተስማሙበት አንድ ጉዳይ ያለ ምእራባውያን እርዳታ ንክች እንደማናደርገው ነበር፡፡ለዚህም ነው እነዚህ ድሀ ሀገሮችን እንረዳለን የሚሉ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት እንደ አይ.ኤም.ኤፍ እና ወርልድ ባንክ ብድርም ሆነ እርዳታ የከለከሉን፡፡

ገና ከጅምሩ በጽናት ታግሎ በማሸነፍ እንጂ በእርዳታ የማያምነው ህዝባዊ መንግስት ከትጥቅ ትግል ጀምሮ የተባበረ ህዝባዊ ክንድ ተአምር እንደሚሰራ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በራሴና በህዝብ ኃይል እሰራዋለሁ በማለት ይፋ አደረገ፡፡ ህዝቡ፤ ግድቡ በኛው ኢትዮጵያውያን መሀንዲስነት፣ በኛው ጉልበትና ገንዘብ የምንሰራው የማንነታችን መለያ፣ የኛው የጣት አሻራ የሚያርፍበት መሆኑን ሲረዳ  ከዳር ዳር ሆ ብሎ ተነሳ፡፡አባይ ከጥንት ጀምሮ ብዙ ብዙ የተባለለት፣ብዙ የተዜመለት፣አፈራችንና ማእድናችንን እንዳሻው እየጠረገ ለጎረቤት ሀገር አልፎም ለግብጽ ሲገብር የኖረ፣እያዩ የሚያዜሙለት ግን ደፍሮ የሚጨብጠው የሌለ ሞገደኛ ወንዛችንን ዛሬ በራሳችን ማረሚያ ቦታ ልናበጅለት ነው፣ኤሌክትሪክ በማመንጨት ሊክሰን ነው ሲባል ከሚመገበው ከጉሮሮው ቆጥቦ ድርሻውን ለመወጣት ሁሉም ድጋፉን መስጠት ጀመረ፡፡እናም የአንድ አመት የግንባታው አፈጻጸም ሲታይ በተያዘለት ዕቅድ እንደሚጠናቀቅ ተረጋገጠ፡፡ ስራው እየተጣደፈ የህዝቡም ተነሳሽነት እየጨመረ ከመምጣቱም በላይ ህዝባችን ለዘመናት ጨፍኖት የነበረው የድህነትና የተረጂነት መንፈስ ከላዩ ላይ በኖ በመጥፋቱ በተሰማራበት ሁሉ ውጤታማ መሆን ጀመረ፡፡

የማይሞከረው ተሞከረ፤ የማይቻለው ተቻለ፡፡ የግብጽ ህይወት፣የግብጽ ስጦታ ሲባል የነበረው አባይ ለኢትዮጵያም ብርሀን ሊሆን ነው ሲባል ገና ካሁኑ ህሊናችን በራ፡፡እናም ዙሪያችንን በመቃኘት በንቃት መራመድ ጀመርን፡፡ምንም የሚሳነን ነገር እንደሌለ ከህዳሴው ግንባታ በመማር አስደናቂ የስራ አፈጻጸሞችና ፈጠራዎች በየዘርፉ መሰማት ጀመሩ፡፡ህሊናው የበራ ህዝብ መንገዱ ብሩህ ነውና፡፡

ዛሬ በየትኛውም ሙያ ዘርፍ ትጉህና ታታሪ ሰራተኞችን እናገኛለን፡፡በማናቸውም የሙያ መስክ የፈጠራ ስራዎች እየተበራከቱ ነው፡፡ በትምህርት ቤት ህጻናት ከቀለም ትምህርቱ በዘለለ የፈጠራ ስራ ባለቤት ሆነዋል ይህንንም የትምህርት ቤት መዝጊያ በአል ላይ በማየት የሚረጋገጥ ጉዳይ ነው፡፡በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፎችም ብንሄድ በዘርፉ ከድህነት ወጥተው ራሳቸውን ከመቻላቸውም በላይ የተለያዩ ማሽኖችን ከሀገር ውስጥ በሚገኙ ማቴሪያሎች አሻሽለው በመስራት በቀላል ዋጋ የሚያከፋፍሉ  ዜጎችን እናገኛለን፡፡ዲግሪ ይዘው ወደ ግብርና ገብተው ምርታማ የሆኑና ለአካባቢው አርሶ አደር  ሞዴል ሆነው ምርታማነትን የሚያስፋፉ ወጣቶችም ተፈጥረዋል፡፡ በህክምናውም ዘርፍ ብዙ አስደናቂ ስራዎችን እንሰማለን፡፡የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ተቀርጾ ባለሙያዎች የነዋሪዎችን በር እያንኳኩ ከማስተማራቸውም በላይ በጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች የሚሰጠው አገልግሎት እየተሻሻለ መቷል፡፡መንግስት አባይን ደፍሮ ከማደፋፈሩም በተጨማሪ በየትኛውም ዘርፍ ለሚፈጠሩ ምርጥ ተሞክሮዎች፣የተሻለ አፈጻጸሞችና የፈጠራ ስራዎች ዕውቅና በመስጠት እያበረታታ ይገኛል፡፡ ሚዲያውም የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማመቻቸት የፈጠራ ሰዎችንና አርቲስቶችን በማወዳደር ላይ ነው፡፡ይህ ደግሞ ለዜጎቹ ይበልጥ ወኔን አጎናጽፏል፡፡

ለአብነት ያህል ከሰሞኑ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አንድ ተአምረኛ ዜና ሰማን፡፡በመዲናችን አንዲት ሴት ተጣብቃ የተወለደች ጥገኛ መንትያ ገላዋን በኢትዮጵያውያን ዶክተሮች በኦፕራሲዮን ተገላገለች የሚል፡፡እስካሁን የዚህ አይነቱ ኦፕራሲዮን በአለም ላይ ሲደረግ ገላቸው ያልጠነከረ ሕጻናት ላይ ሲሆን እስካሁን ይሄ ተሳክቷል ሲባል ሰምተን አናውቅም፡፡በኛ ሀገር ግን ያውም ሰውነትዋ የጠነከረ ትልቅ ሴት ለብዙ አመት ተሸክማው የነበረችውን ጥገኛ መንትያዋን ተገላግላ በሰላምና በጤንነት ላይ ትገኛለች በማለት የተሳካ ህክምና መካሄዱ ሲሰማ  የሚደንቅ ነው፡፡ዶክተሮቹ  እንደተለመደው ከአቅማችን በላይ ነው ብለው ለምን ወደ ውጪ ሪፈር አልጻፉም፡፡እንዴት ደፍረው ይህን ያህል ከባድ ኦፕራሲዮን አደረጉ ብለን ብንጠይቅ መልሱን ከአንደበታቸው እናገኛለን፡፡ዶክተሮቹ ምን አሉ "የማይደፈረው አባይ መደፈሩ እኛም ምንም የማይቻል ነገር የለም በማለት ልንደፍር ችለናል" ፡፡

እርግጥ ነው ዶክተሮቹ እንዳሉት የማይደፈረው አባይ ተደፍሯል፡፡የውሃ ማማዎችን ተሸክመን ዝናብ ስንጠብቅ የነበርን ፣ለምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የሚተርፍ  የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እየቻልን ጉልበታችንን አቅፈን ስንራብ የነበርን ህዝቦች ዛሬ በታላቁ ህዳሴ ግድብ መጀመር ወኔያችን ተነሳስቷል፡፡ምንም እንኳን በአፍሪካ በራስዋ ሀገር ዜጎች አቅም የተሰራ ግድብ ባይኖርም እኛ ከአለም ድሃ ስንባል የኖርን ህዝቦች ይህን ገድል በመፈጸም ታሪክ ሰሪነታችንን ለማረጋገጥ ተነሳስተናል፡፡ ዛሬ ጀግንነት ማለት ለዘመናት አንገት

ያስደፋንን ድህነትና ኋላቀርነት ማስወገድ እንደሆነ በርቶልናል፡፡የታላቁ ህዳሴ ግድብም በዚህ ጀግና ህዝብ ልብ ውስጥ ተስሏል፡፡ ጠቅላላ የሀገሪቱ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክንዳችንን እንደ አንድ ክንድ አንስተናል፤ ያውም የተገመደ ጠንካራ ክንድ፡፡ ባለም ምናልባትም በትልቅነቱ ሰባተኛ ደረጃ የተሰጠውን ግድብ ያለማንም ጣልቃ ገብነት እኛው በኛው እንሰራዋለን፡፡ጀምረነዋል እንደጀመርንም እንጨርሰዋለን፡፡

የታላቁ ህዳሴ ግድብ የፈጠረው መነቃቃት በግድቡ ብቻ የሚቆምም አይደለም፡፡ ለዘመናት አሸልቦ የነበረው ታላቅ ህዝብ የህዳሴውን ግድብ መሸጋገሪያ በማድረግ ሀገሪቱን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ እንደሚያደርሳት በገሀድ የሚታየው ቁርጠኝነት አረጋግ∨ል፡፡ለህዳሴው ግድብ እየተረባረብን ሌሎችንም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ከግብ እናደርሳለን፡፡ለዳር ድንበሩ ህይወቱን ሲገብር የኖረ ህዝብ ጉልበቱንና ገንዘቡን አስተባብሮ ሀገሩን ለመቀየር ምን ይሳነዋል? ድህነትና ኋላቀርነት በኛ ይብቃ ብለን ተነስተናል፡፡ ለትውልድ ብሩህ ጊዜ ለማውረስ ዛሬ በተፈጠረልን አጋጣሚ ተጠቅመን በጋራ ህዝባዊ ክንዳችን ልማትን እናፋጥናለን፡፡ለዚህም የተጀመረው ህዝባዊ ተነሳሽነት ለህዳሴያችን ጉዞ ስኬት አመላካች ነው፡፡ታሪክ የምንሰራበት ጊዜ አሁን በመሆኑ ሳይመሽ በብርሀኑ እንሩጥ፡፡

እርስዎስ በዚህ የህዳሴ ዘመን ምን የተለየ ነገር ሊሰሩ አስበዋል? ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እስከፍጻሜው በመቆም ለትውልድዎ ታሪክ ያቆዩ!